## ዓጋሮች - המשך פעילויות בעקבות הסיפור




በ: ሊያ ናኦር
ምሳሌዎች: ጊሊ-ሊ አሎን ኮሪኤል
הוֹצָאָה: ספרית פועלים
የእድሜ ክልል: ታዳጊዎች

קְרִיאָה

**ለቤተሰባዊ ንባብ የሚሆን ጠቃሚ ምክር- ልምድን ማጋራት**

ብዙ መጻህፍት የህፃናትን የእለት ተእለት ሕይወት ላይ የሚገጥሚቸውን ተግዳሮቶች ይገልፃሉ፡- የማካፈል ችግር፣“ የመሰናበት ችግር፣ ከቀን ወደ ማታ የመሸጋገር ፈተናና ሌሎች ብዙ። ታዳጊው ፈተና እየገጠመው መሆኑን ስትረዱ ከጉዳዩ ጋር የተያያዘ መጽሐፍ መርጣችሁ አብራችሁ አንብቡ። መጽሐፉ ስሜትንና ልምዶችን እንድታካፍሉ ይጋብዛል።

የመለ

ያ፣ የማበረታቻና የመቋቋሚያ ሃሳቦችን ማቅረብ ይችላል።

ሊያ ናኦር – በ1935 በሄርጼሊያ ተወለደች። ለህፃናት መጽሃፎችን፣ ድራማዎችን፣ ስክሪፕቶችንና መዝሙሮችን የጻፈች ሲሆን ብዙ መጽሃፎችን ወደ ዕብራይስጥም ተርጉማለች። ከእነርሱም መካከል ተከታታዩ “”ዶክተር ሱስ”” ”ይገኙበታል። መጽሐፎቿና ትርጉሞቿ ብዙ ሽልማቶችን አሸንፈዋል።

שִׂיחָה

**?የእኔ ምንድን ነው የእኛስ ምንድን ነው**

ለእያንዳንዱ የየራሳቸው ከሆኑት ነገሮች በተቃራኒ ለሁሉም የቤቱ አባላት የተለመዱትን የጋራ ነገሮች ላይ መወያየት ትችላላችሁ። ለምሳሌ፡- “ሁሉም ሰው የራሱ የጥርስ ብሩሽ አለው – የእርስዎ የጥርስ ብሩሽ ምን ይመስላል?” “ቤቱ ?አንድ ላይ የሁላችንም ነው፤ በእኛ ቤት ውስጥ ማን ማን ይኖራል

מִשְׂחָק

**መተወንና መቀያየር**

በእንስሳት አሻንጉሊቶች እርዳታ መጽሐፉን መተወንና አንድ ላይ መዝናናት ትችላላችሁ፡- በመዝሙሩ መሰረት አሻንጉሊቶችን በመካከላችሁ ቀያይሩ፣ በተደጋገመው ዓረፍተ ነገር ውስጥም “ከዚያም በቅርብ ጊዜ በሁሉም ውብ ነገሮች ላይ ዓጋሮች እንሆናለን” የሚለው ላይ አሻንጉሊቱን አንድ ላይ በማያያዝ አጋርነት ምን እንደሆነ አሳዩ።

כְּלָלִי

**ምስሎችና እንስሳት**

ድመት፣ እርግብ፣ ኤሊ፣ ቡችላና ጫጩት – ሁሉም በአንድ መጽሐፍ! ምስሎችን መመልከት፣ አንድ ላይ አንድን እንስሳ መምረጥ፣ ድምፁን ማስመሰልና በመጽሐፉ ውስጥ በተገለጸው መሰረት ማስመሰል ይቻላል። ለምሳሌ፡- ኤሊ ከመረጡ “ሙሉ ቤት በጀርባ ላይ” – ትራስ በጀርባዎ ላይ በማስቀመጥ በአራት እግሮች መሄድ ይችላሉ። በጅራቱ ?ላይ ጭራ ያለው ቡችላ እንዴት ያወዛውዛል

הַשְׁרָאָה

פינטרסט

ለተጨማሪ ሰርፕራይዞች፣ ተነሳሽነቶችና ሃሳቦች ወደ ፒጃማ ቤተ መጻህፍት ፒንተረስት ውስጥ ይግቡ

עוד פעילויות באתר ספריית פיג'מה www.pjisrael.org